የሰ/መ/ቁ. 65330

ሰኔ 30 ቀን 2003 ዓ/ም

ዳኞች፡-ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትሕ ሚኒስቴር

**ተጠሪ፡-**1. አቶ ተክሌ ጋርደው

2. አቶ ሐይማኖት አባተ

3. አቶ ታረቀኝ ወልዴ

4. አቶ ተሾመ አረጋይ

5. አቶ አብነት ደምሰው

6. አቶ አቡኪያ ቤኛ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር00944/2002 ሚያዚያ 15 ቀን 2002 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ አስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔ ባግባቡ ነው ሲል በፍ/ይ/መ/ቁጥር 55990 ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ለሰበር አቤቱታው ምክንያነት የሆነው ጉዳይም አገልግሎትና የእድሜ መስፈርቱን የማያሟሉ ሰራተኞች ከስራ ሲሰናበቱ የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ እንዲያገኙ ሲደረግ በክፍያው ላይ የስራ ግብር ሊቀነስ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ላይ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስራ ግብር ሊቀነስ አይገባም በማለት ውሳኔ በመስጠታቸው ነው፡፡በዚህ መሰረት በቀረበው አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለው ይህንኑ ነጥብ ለማጣራት ሲሆን አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ ተመርምሯል፡፡ ለዚህም ስለገቢ ግብር የሚደነግገውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 መመልከቱ

ተገቢ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 10(1) ስር በግልፅ እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ የገቢ ግብር ይከፍላል በማለት ተቀምጧል፡፡ ከግብር ክፍያ ነጻ የሆኑትን አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 13 ላይ በዝርዝር ሲገልጽ አሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ጉዳይ አይነት በግልፅ ከስራ ግብር ነፃ ስለመሆኑ አይጠቅስም፡፡ ይህ አንቀፅ ከግብር ክፍያ ነፃ የሆኑትን ከዘረዘራቸው ውስጥ ማናቸውንም አይነት የጡረታ ጥቅም፣ወይም በተቀባዩ ሰው ላይ በደረሰ የአካል ጉዳት ካሳ ወይም በሌላ ሰው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ የሚሰጥ የካሳ ክፍያ የሚሉት ይገኙበታል፡፡የካሣ ክፍያ ሲባልም በሕጉ ላይ በግልፅ እንደተመለከተው በደረሰ የአካል ጉዳት ወይም በደረሰ የሞት አደጋ የሚሰጥ የካሳ ክፍያ የሚመለከት እንጂ ማናቸውንም የካሳ ክፍያ ሁሉ ከግብር ነጻ መሆኑን የሚጠቅስ አይደለም፡፡በመሰረቱ የስራ ግብር የሚከፈለው ማንኛውም ሰው በመቀጠር ምክንያት በሚያገኘው ማናቸውም ገቢ ላይ ስለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 10(1) በግልፅ ያሰፈረው ሲሆን አዋጁ ገቢን አስመልክቶ በሰጠው የትርጉም ክፍል ላይ ገቢ ማለት ማናቸውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማናቸውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት በማናቸውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው በስሙ የተያዘለትን ወይም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ እንደሚጨምር እንዲሁም ግብር የሚከፈልበት ገቢ ማለት ደግሞ በአዋጁና በአዋጁ መሰረት በሚወጡት ደንቦች መሰረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው የገቢ መጠን መሆኑ አዋጁ  በአንቀጽ 2(10) እና 1(11) አስፍሯል፡፡ በመሆኑም ለተጠሪዎች ይከፈል የተባለው የመቋቋሚያ ክፍያ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት አላገኘንም፡፡በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ